Government of **Western Australia**
Department of **Health**

# የማሞግራፊ ማጣሪያ ማስታወሻ

BreastScreen WA
WA's only accredited screening service

## ወደ ምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ ክሊኒክ እንኳን ደህና መጡ...

ማጣሪያውን ከማድረግዎ በፊት፤ እባክዎን ይህንን ስለማሞግራም የሚያስረዳውን ጠቃሚ መረጃ አንበበው ተያይዞ የሚገኘውን ፈቃድዎን ለመስጠትዎ የሚመሰክረውን ጽሑፍ ይፈርሙ። ጥያቄ ካለዎት የማጣሪያው ክፍል ሠራተኞች ሊረዱዎት ይችላሉ። እባክዎን ያስታውሱ፤ የማጣራቱ ድርጊት እንዳይደረግልዎት ከፈለጉ በማንኛውም ጊዜ ማስቆም ይችላሉ።

### ስለ ጡት በሽታ የማጣሪያ ፕሮግራም

የጡት በሽታ የማጣራት ፕሮግራም አላማ በጡት ነቀርሳ ምክንያት የሚደርሰውን ሞት ለመቀነስ ነው። በአሁኑ ወቅት፤ በመነካካት ለማግኘት የማይቻለውን የጡት ነቀርሳን ለማግኘት የሚረዳው ዋናው ዘዴ ማሞግራም (የራጅ ምርመራ) ነው። ቀደም ብሎ በምርመራ የተገኘ የጡት ነቀርሳ በህክምና የመዳን እድሉ በጣም ጥሩ ነው።

የምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ ፕሮግራም ትኩረት፤ የጡት ነቀርሳን ቀደም ብሎ ለመለየት ነው። በማሞግራም ላይ የታየው ከጡት ነቀርሳ ጋር ያልተያያዘ ማንኛውም ለውጥ አይዘገብም።

ወቅታዊው የህክምና መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ማጣሪያው በጣም የሚረዳው እድሜአቸው ከ50 እስከ 74 ዓመት ለሚገኙ ሴቶች ነው። በጡት ነቀርሳ የመያዝ እድሉ ከእድሜ ጋር ይጫምራል። ወደ 70% የሚጠጋው የጡት ነቀርሳ የሚደርሰው እድሜአቸው ከ50 ዓመትና ከዚያ በላይ በሆነ ሴቶች ላይ ነው። በየጊዜው የሚደረግ የማጣሪያ የማሞግራም ምርመራ በነዚህ ሴቶች ላይ የሚደርሰውን የሞት ቁጥር 30% ይቀንሰዋል። የማሞግራም የማጣሪያ ምርመራ፤ እድሜአቸው ከ50 ዓመት በታች ለሆኑ ሴቶች ጠቀሜታው ዝቅ ያለ ነው።

### የማሞግራም ምርማራ የሚደረገው እንዴት ነው?

**እስከወገብዎ ድረስ ያለውን ልብስ አውልቀው ፒጃማ እንዲለብሱ ይጠየቃሉ። በራዲዮግራፍ የሰለጠነች ሴት ባለሙያ ማመግራፉን ታነሳዎታለች።**

ማሞግራሙ በሚደረግበት ጊዜ ጥራት ያለው ፎቶግራፍ ለማንሳት ጡትዎን ከመሳሪያው ጋር ለጥቂት ሰኮንዶች በጣም ይጫኑታል። ምናልባትም አይመችዎት ይሆናል።

አብዛኛውን ጊዜ እያንዳንዱ ጡት ሁለት ሁለት ፎቶግራፍ ይነሳል። ይሁንና ተጨማሪም ሊያስፈልግ ይችላል።

### ማሞግራሙን የሚያነበው ማነው?

**የማሞግራሙ ውጤት ላይ የሚደረሰው ቢያንስ ሁለት በመስኩ ባለሙያና ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ዶክተሮች (ራዲኦሎጂስቶች) ካነበቡት በኋላ ነው። ሁሉም ማሞግራሞች የሚነበቡት በገለልተኝነት ነው። አልፎ አልፎ፤ ሁለቱ ራዲኦሎጂስቶች ካልተስማሙ ሶስተኛ ራዲኦሎጂስት እንዲመለከተው ይደረጋል።**

### ድጋሚ የራጅ ምርማራ ቢያስፈልገኝስ?

አልፎ አልፎ በራዲኦሎጂ ባለሙያ የተነሳው ፎቶግራፍ ግልጥ ሆኖ ካልታየ ድጋሚ የራጅ ምርመራ እንዲደረግ ይጠይቃል። ይህ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተመልሰው እንዲመጡ የስልክ ጥሪ ወይንም ደብዳቤ ይደርስዎታል።

## ውጤት ስለማሳወቅ

**ለአብዛአኛዎቹ ሴቶች በ14 ቀናት ውስጥ ሁሉም ውጤት ጥሩ እንደሆነ በደብዳቤ ይገለጥላቸዋል። ሴቶችን ለተጨማሪ ምርመራ መጥራት ያልተለመደ አይደለም። ይህ አስፈላጊ ከሆነ፤ የምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያው ምርመራ ክፍል ነርስ ሰልክ በመደወል ስለሁኔታው ታወያይዎታልች። አብዛኛው ምርመራ ምንም ችግር ስለማያሳይ ተጫማሪ ምርመራ ማድረግ አያስፈልግም።**

በከተማ የሚኖሩና የማጣራት ምርመራውን ያደረጉ ሴቶች፤ በፕሮግራሙ የግምገማ ማእከል ተጨማሪ ማሞግራም ለማድራግ ወይንም፤ አስፈላጊ ከሆነ በድጋሚ ምርመራ ለማድረግ ቀጠሮ ይስጣቸዋል።

የማጣራቱ ተግባር በክፈለ ሃገር በተንቀሳቃሽ የህከምና መኪና ላይ ላደረጉ ሴቶች፤ ለምቾታቸው ሲባል ተጨማሪ የማሞግራም ክትትል በተንቀሳቃሽ የህክምና መኪና ላይ ይደረግላቸዋል።

**እባክዎን ያስታውሱ፡** የምዕራብ አውስትራሊያ የጡት በሽታ ማጣሪያ የማሞግራሙን ውጤት ከሌላ ተጨማሪ ፊልም ጋር ለማመሳከር ይይዘዋል።

**የማሞግራም ምርመራ ምን ያህል ሁነኛ ነው?**

**የማሞግራም ምርመራ 90% የሚሆነውን የጡት ነቀርሳ ሊያሳይ ይችላል። በማሞግራም የማይታዩ አንዳንድ የነቀርሳ አይነቶች አሉ። ወጣት ሴቶች ወይንም የሆርሞን መተካት ህክምና ላይ ያሉ ሴቶች፤ የጡት ህዋሳቸው በእድሜ ከገፉ ሴቶች ይልቅ ደንደን ያል ስለሆነ ነቀርሳውን በማሞግራም ለማየት በጣም ያስቸግራል። በዚህም ምክንያት ወጣት ሴቶች ተጨማሪ ምርመራ ያስፈልጋቸው ይሆናል። ይህም ከወጣት ሴቶች ጡት ላይ ቁራጭ ሥጋ በመወሰድ (ባዮፕሲ) ምርመራ ማድረግንም ይጨምራል። ምክንያቱም፤ የማሞግራሙ ምርመራ ነቀርሳውን ለይቶ ለማሳየት ስለሚያስቸግር ነው።**

በተማሳሳዩም፤ የማሞግራም ውጤት በመጀመሪያ ሊያሰጋ ይችላል። ይሁንና ተጨማሪ ምርመራ ሲደረግ የሚያሰጋ ችግር አይታይም።

የማሞግራም ምርመራ ማድረጉ በራሱ ከነቀርሳ በሽታ አያድንም። ይሁንና ቀደም ብሎ ማወቁ ውጤታማ የሆነ ህክምና ለማግኘት ያስችላል።

**ማሞግራም ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ወይ?**

**አልፎ አልፎ የማሞግራም ምርመራውን ለማድረግ ጡትን በጣም መጫኑ ጊዜያዊ እብጠት ወይንም መቁሰል ሊገጠም ይችላል። ይህም በጡት ህዋስ ላይ ዘላቂ ጉዳት አያመጣም።**

እያንዳንዱ ማሞግራም በጣም ዝቅተኛ የሆነ የራጅ ጨረር ይጠቀማል። ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች ከራጅ ጨረር መጋለጥ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ችግር በጣም ጥቂት እንደሆነ ያመለክታሉ። የማሞግራም ምርመራ ጥቅም ከጉዳቱ ጋር ሲተያይ በጣም ያመዝናል።

| |
|---|
| እርጉዝ ለመሆናቸው የሚጠራጠሩ ሴቶች የማሞግራም ምርመራ ማድረግ ጥሩ አይደለም። ምናልባት እርጉዝ የመሆን እድሉ ከለዎት እባክዎን ለእንገዳ ተቀባይዋ ወይንም ለራጅ አንሺው በቅድሚይ ይናገሩ። |

**የጡት እባጭ ወይንም የጡት ችግር ቢኖርብኝ ምን ይሆናል?**

በጡትዎ ላይ እባጭ ተመልከተው ከሆነ፤ እንዲሁም ከጡትዎ ጫፍ ፈሳሽ የሚወጣ ከሆነና ወይንም ሌላ ለውጥ ተስምቶዎት ከሆነ፤ እባክዎን ማሞግራሙን ከማድረግዎ በፊት ለራጅ አንሺዋ በቅድሚያ ያስታውቁ። ምንም እንኳን የማሞግራሙ ውጤት ችግር ባይኖረውም፤ ስለአዩአቸው ለውጦች ሃኪምዎን ማማከር በጣም አስፈላጊ ነው።

**የቤተሰብ ሃኪሞን ዝርዝር መረጃ መስጠት ለምን ያስፈልጋል?**

አስፈላጊው የጤና እንክብካቤ እንዲደረግልዎት የቤተሰብ ሃኪምዎ ስለእርስዎ አስፈላጊው መረጃ ሁሉ እንዲደርሰው/ሳት ያስፈልጋል። የማሞግራሙን ውጤት ለእርሱ/ለእርሷ መላክ እንፈልጋለን። ማሞግራም ካደረጉ በኋላና በቀጣዩ መካከል፤ በየጊዜው ጡትዎን እየነካኩ መመርመር በጣም አስፈላጊ ነው። ለውጥ ካዩ ወዲያውኑ ለሃኪምዎ ይንገሩ። በየጊዜው ጡትዎን በሃኪምዎ እንዲያስመረምሩ እናሳስባለን።